የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር
Ref. No. ..............................

ቀን
Date ..............................

ህዳር 19፣2001 ዓ.ም

# የጎዳና ላይ ቅስቀሳን አስመልክቶ ከመንግሥት እየደረሰብን ያለውን ጫና እንቃወማለን።

## (ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት - መኢአድ የተሰጠ መግለጫ)

መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መስከረም 9/1995 ዓ.ም ህጋዊ ፈቃድ አውጥቶ ሰላማዊ ትግል በማድረግ ላይ የሚገኝ ፓርቲ መሆኑ ይታወቃል። ፓርቲያችን ህገመንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ በአዲስ አበባ ከተማ በሁሉም ክፍለ ከተሞች የጎዳና ላይ የመኪና ቅስቀሳ ለማካሄድ ዕቅድ አውጥቶ ለሚመለከታቸው አካላት አሳውቋል።

በዚሁ መሠረት ፓርቲያችን በአዲስ አበባ አስተዳደር ለፍትህና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ በቁጥር መለ/3/145/2001 ህዳር 5/2001 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የጎዳና ላይ ቅስቀሳ ማድረግ እንደሚፈልግ አሳወቆ፤ ቢሮውም ለጎዳና ላይ ቅስቀሳ የተለየ ፈቃድ የማያስፈልገው በመሆኑ የምርጫ ቦርድ የሕጋዊነት የምስክር ወረቀት ይዞ ሊቀሰቅስ እንደሚችል ገልፇል።

መኢአድ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ደብዳቤ በመጻፍ በአዲስ አበባ ውስጥ የጎዳና ላይ ቅስቀሳ የሚያካሂድ መሆኑን ገልጾ አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያደርግ ጠይቋል። የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽንም ፓርቲው ለቅስቀሳ በመረጣቸው ቀናት አዲስ አበባ ውስጥ ሌሎች ህዝባዊ ሥራዎች የሚከናወኑ በመሆናቸው የቀን ለውጥ እንዲደረግና የቀን ለውጦችንም መኢአድን ለኮሚሽኑ እንዲያሳውቅ ማሳሰቢያ ሰጠ። በዚሁ መሰረት መኢአድ ከህዳር 18፣2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 21፣2001ዓ.ም ድረስ ቅስቀሳውን እንደሚያካሂድ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ አሳውቋል።

መኢአድ ህጋዊ የሆነ መንገድን በመከተል መሔድ እስከሚገባው የመንግስት አካላት ድረስ በመሔድ ለሰላማዊ ትግል ያለውን ቁርጠኝነት በመግለፅ ህዳር 18,2001 ዓ.ም ቅስቀሳ የጀመረ ቢሆንም ፓርቲው በሚያካሂደው ቅስቀሳ የተደሰተና ድጋፉን ለፓርቲው እየገለፀ ያለውን ህዝብ የተመለከተው የአዲስ አበባ ፖሊስ በቤተልና በሳሊተ ምህረት አካባቢ የቅስቀሳ ሥራችንን ሲያውክ ቆየ። እንዲሁም ህዳር 19,2001 ዓ.ም የፓርቲውን የቅስቀሳ ቡድኖች እና የሚንቀሳቀሱበትን ሁለት መኪኖችን ጭምር በየካ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ጣቢያና በላዛሪስት ትምህርት ቤት አጠገብ በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች አስረዋል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ፍቃድ መስጠትም ሆነ መከልከል የሚችልበት አንዳችም የህግ መሠረት ሳይኖረው የፓርቲው መልዕክት ያለበትን የድምፅ ቅስቀሳና የቴዲ አፍሮ ዘፈንን በመከልከል ፈቃጅና ከልካይ በመሆን አለአግባብ በፓርቲው አባላት ላይ እስራት ፈፅሟል።

ፖሊስ ሁሉንም ፓርቲዎች በእኩል ማገልገልና ጥበቃ መስጠት ሲገባው ምንም አይነት ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው እገዳና እስራት መፈፀሙ ህገመንግስታዊ ስርዓቱን የጣሰ ህገወጥ ተግባር ነው።

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ፓርቲዎች በሰላማዊ መንገድ የመሰብሰብ ዓላማቸውንና ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ የማሣወቅ መብት ሰጥቷቸዋል።

በዚሁ መሠረት መኢአድ ሕገ መንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ በሚያካሂደው የጎዳና ላይ ቅስቀሳ ከመንግስት እንግልትና ወከባ እየተፈፀመብት ይገኛል።

መንግስት በአሁኑ ወቅት እየወሰደ ያለው እርምጃ ከዚህ ቀደም ከሚያደርገው የማዋከብና የማሰር ተግባር ያልተቆጠበ መሆኑንና ለወደፊቱም ቢሆን ፓርቲያችን የሚያደርገውን የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ለመግታት የተዘጋጀ መሆኑን አመላካች ነው።

በመሆኑም አባሎቻችን፣ ደጋፊዎቻችንና በአጠቃላይም ህዝባችን እንዲሁም ዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ይኸንን ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ ግንባታ የምናደርገውን ትግል እውን እንዲሆን ከጎናችን በመቆም እየተፈፀመብን ያለው ወከባና እስራት እንዲቆምና ሰላማዊ ትግሉ እንዲቀጥል የበኩላችሁን ታደርጉ ዘንድ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ጥሪ ያቀርባል።

በሰላማዊ ትግል የሚገኝ ውጤት
ሀገርና ህዝብ ያኮራል!!